የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄን
Ginbot 7: Movement for Justice Freedom and Democracy

# የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄን መመሥረት በመሚልከት የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

## ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ህዝብ የዘመናት የፍትህና የነፃነት፣ ጥማትና ተጋድሎ ዛሬም እንደቀጠለ ነው። ከሶስት አመታት በፊት መንግስትና የተቃዋሚ ድርጅቶች ባደረጉት ስምምነት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በነፃነት ድምጹን እንዲሰጥና፣ ሃገሪቱን ሲንጥ ለኖረው የፖለቲካ ስልጣን ጥያቄ እልባት እንዲገኝለት ተወሰነ። በውሳኔውም መሰረት ከ25 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ለምርጫ ተመዘገበ። ግንቦት 1997 ዓ.ም ተመዝጋቢው ህዝብ ካርዱን ይዞ በየምርጫው ጣቢያው ለአስር ሰአታት ቆሞ መረጠ። ይህ በፍጹም ሠላምና መረጋጋት የተካሄደ ምርጫ፣ በዋና ዋና ከተሞች ለተቃዋሚው ድልን ማጎናጸፉ ሲታወቅ፣ ግንቦት 8 1997 ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከምሽቱ 3 ሰኣት ላይ በመንግስት ተሌቪዥን ላይ ወጥተው‹ የአስቸኳይ ጊዜ አወጅ አወጁ። በመዲናዋ አዲስ አበባ መሰብሰብና መሰለፍ ወዘተ አገዱ። የሰራዊቱን የፖሊሱንና የደህንነቱን ሃይል እዝ በስራቸው ጠቀለሉ። በየገጠሩ የነበሩትን የድምጽ መስጫ ኮሮጆች በቁጥጥራቸው ስር አደረጉ። ከአንድ ቀን በኋላም 10 በመቶ የሚሆነው የመራጭ ድምጽ ገና ሳይቆጠር "ገዥው ፓርቲ አሸንፏል" ብለው አወጁ:: ሰኔ አንድ ቅን የሰላመዊ ሰልፈኞችን ደም አፈሰሱ።

ገዥው ፓርቲ ተደናግጧል፣ ከስልጣን ለመውረድ ዝግጁ አይደልም የሚል ግምገማ ላይ የደረሱት ሁለቱ የተቃዋሚ ድርጅቶች በጋራ ለጥምር መንግስት ምስረታ ያደረጉትን ጥሪ ወያኔ/ኢህአዴግ አልቀበል አለ። ቅንጅቱ በጥቅምት 1998 "ይሁን፣ ለሚቀጥሉት አምስት አመታት ግዛ፤ ግን ቀጣዩ ምርጫ ተመሳሳይ እክል እንዳይገጥመው በነዚህ መሰራተዊ ጉዳዮች ላይ እንስማማ" ብሎ ላቀረበለት ባለ 8 ነጥብ፣ ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የሚጠቅሙ ሃሰቦች ምላሹ በእብሪት የቅንጅትን መሪዎች ወህኒ በመወርወር ትግሉን ለመደፍጠጥ መሞከር ሆነ። ቀጥሎም በእዚሁ ሳምንት እስከ አፍንጫው የታጠቀውን የአጋዚ ጦራቸውን በማዝመት በአዲስ አበባ ብቻ በትንሹ 193 ዜጎችን ህይወት ቀጠፉ። በገጠርና በሌሎች ከተሞች የተቀጠፈውን የለጋ ወጣት ህይወት ቤቱ ይቁጠረው።

ያሰሯቸውን የቅንጅት መሪዎች ለ21 ወራት ካማቀቁ በኋላ፣ በፍጹም  አይን አውጣነት ‹ በሃገር ክህደትና በዘር ማጥፋት ወንጀል› ከሰው የእድሜ ልክ እስራት ካስፈረዱ በኋላ "አጥፍተናል ማሩን የሚል ሰነድ ካልፈረማችሁ አትለቀቁም" ብለው፣ እራሳቸው የመረጧቸውን ሽማግሌዎች  አስዋሽተውና አዋርደው፣ የአእምሮ ተጽእኖ በማድረግ ተሳለቁ። የቅንጅትን ህጋዊነት ከከለከሉ በኋላ ባደረጉት የቀበሌና የአዲስ አባባ የፓርላማ ማሟያ ምርጫ ከሶስት አመታት በፊት የተነፈጉትን የህዝብ ድምጽ፣ በተነፈጉት መጠን እንዳሻቸው እየሰፈሩ በመውሰድ አሸንፈናል ብለው በህዝብ ብሶት አላገጡ። ህዝብ የማዋረዱና ክብሩን የመገሰሱ ትእይንት እንደቀጠለ ነው። የህዝብ ሲቃና ሰቆቃ በማንጎራጎር፣ የህዝብን ተስፋና ምኞት በማመላከት ታወቀውን የአንድነት፣ የፍቅርና የመቻቻል ቅዱስ ድምጽ የሆነውን ቴዲ አፍሮን በእስር በማንገላታትና የታላቁ ቴዎድሮስ የትውልድ ስፍራ የሆነችውን የቋራን ቀበሌዎች ለሱዳን አሳልፎ በመስጠት፣ የእብሪትና የክህደት ተውኔቱ ቀጥሏል። ነገሩ ህዝብን "ምን ትሆናለህ" የሚል  የባለጌ ስድብ ነው።

ይህ የውርደት ትዕይንት መበራከት ነው ለግንቦት 7 ንቅናቄ መነሻ የሆነው። ለክብራችን እንሞታለን ነው የምንለው። በጥቅምት 1998 ያነሳነው የህዝቡን ስልጣን የሚያረጋግጥ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር አጀንዳ አሁንም ህያው ነው‹ ለማለትም ነው‹ የግንቦት 7 ንቅናቄ›ን ያቋቋምነው። ሃገራችን ኢትዮጵያ ወደተደላደለ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንድትሸጋገር መርዳት ነው የንቅናቄያችን ቀዳሚ ጥረት። ይህንንም፣ በአንድ ፓርቲ አቅም ብቻ፣ ወይም በአንድ የፖለቲካ ርእዮተ-አለም የሚያምኑ ሃይሎች ብቻቸውን ተሰባሰበው እውን የሚያደርጉት ሳይሆን፣ የሃገሪቱ የፖለቲካ እጣ ያገባናል የሚሉ ሃይሎች ሁሉ በጋራ መክረው በሚደርሱበት የጋራ ስምምነት ነብስ የሚዘራ ነው። ይህንን የማስተባበር ትኩረት በመስጠት፣ ንቅናቄያችን በመላ አቅሙ ይረባረብብታል። ተስፋ የሚሰጡ ምልክቶችንም ገና ከአሁኑ እያየን ነው።

በሃገራችን የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በደል የሚፈጽመውም መንግስት በውስጣዊ አቅሙ ብቻ ሳይሆን፣ ለምእራቦች በሚያበረክተው እሽከርና የሚያገኘውን የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የስልጠናና የጥቅም ድጋፍ ይዞ በመሆኑ፤ ይህ የምእራቦች ድጋፍ ዴሞክራሲን ከማራመድ ጋር የተቆራኘ እንዲሆን የሚወተውት አለምአቀፍ የኢትዮጵያውያን ትግል እንዲበራከት መቀስቀስና ማደራጀት፣ የምእራብ ሃገር ዜጎች በመንግስታቶቻቸው ላይ ተገቢውን ተጽእኖ

እንዲያደርጉ ለማድረግ የሚያስችል የ "ኢትየጵያን እወቅ" ዘመቻ ማጧጧፍም ሌላው ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የሚሰለፍበት  መስክ እንዲሆን "የግንቦት 7 ንቅናቄ"ታላቅ የቅስቀሳና የማደራጀት ተግባራትን የመፈጸም መርሃ-ግብረም አለው።

ንቅናቄያችን ገና ከጅማሮው ለወዳጅም ለጠላትም ይፋ የሚያደርገው ነገር ቢኖር፣ በኢትዮጵያችን ላይ የሰፈነውን ብካይና ውርደት ለማምከን፣ ትግሉ አስፈላጊ ሆኖ ካገኛቸው፣ በዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረትና በመብት መከበር ላይ የቆመ የጋራ ሃገር በመገንባት ላይ የጠራ አቋም ካላቸው ጋር ሁሉ ለመተባበረና ለመረዳዳት፣ እርዳታና ስልጠና ለመቀበልና ለመስጠት፣ በአመራር እጦት ምክንያት ችግር የደረሰባቸውን ትግሎች ሁሉ ለማስተባበርና አቅማቸውን ለመገንባት፣ የመንግስት ይሁንታና ፈቃድ የማይጠይቅ መሆኑ ጭምር ነው። ወያኔ/ህአዴግ ሱማሌን እየወረረ፣ ለሱዳን መሬት እየሰጠ፣ ሃገራችንን ያለባህር በር እያስቀረ፣ ወደ ሰልጣን ለመውጣትም ሆነ፣ በስልጣን ለመቆየት የሃገር ክህደት ደባ ሲፈጽም፣ ንቅናቄያችን በሞራል የበላይነት ስም እጁን ኣጣጥፎ እንደማይቀመጥና፣ ትግሉን በአንዲት ጋትም ፈቅ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች ሁሉ ከመውሰድ እንደማይታቀብ ይፋ ማድርግ ይፈልጋል።

ንቅናቄያችን የሚከተለው የትግል መስመር ሁሉን-አቀፍ ነው። የምንፈለገውን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመመስረት ኢህአዴግንም የጨመረ የጋራ ውያይትና ድርድር ማድረግ ከተቻለ፣ አሁንም ለእዚያ ቅድሚያ ይሰጣል። ምን ግዜም እንደዚህ አይነት የሰከነ ውይይትና ድርድር ለማድርግ በሩ ብቻ ሳይሆን ልቡም ክፍት ነው። ይህ ግን ዝም ብሎ ልመና አይደለም። ለሁላችንም ይበጀናል የሚል የሰከነ ጥሪ ነው። የውይይትና የድርድር ጥሪያችን ግን በምንም አይነት ለፍትህ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ያለንን ፍላጎትንና እሱንም ለማግኘት ያለንን እልህ የተቀላቃለበት ሁሉን አቀፍ ትግል የሚጎትት ወይንም የሚያዘናጋ አይሆንም።

በደል የሰለቸው፣ ውርደት ያስመረረው፣ ነጻነት የናፈቀው ኢትዮጵያዊ ሁሉ አብሮን እንደሚታገል፣ በዚህም የጋራ ትግል ነጻነታችንን በአጭር ግዜ ውስጥ እንደምንጎናጸፍ ለአናድ አፍታ እንኳን አንጠራጠርም።

ግንቦት ሰባትን መቼም አንረሳውም
የግንቦት ሰባት መንፈስ ያሸንፋል።